# በኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ
# የብሄራዊ ደህንነት ምክር ቤት

## የምክር ቤቱ አስቸኳይ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ

የስብሰባው ቀን: 15/10/2004
የስብሰባ ሰአት: ከምሽቱ 3:00
የስብሰባ ቦታ: የኢትዮጲያ ፌ/ዴ/ሪ/ ጠ/ሚኒስትር ጽ/ቤት፣ አዲስ አበባ

በስብሰባው ላይ የተገኙ:

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1. | አቶ መለስ ዜናዊ | ጠ/ሚንስትር | ሰብሳቢ |
| 2. | አቶ ኃ/ማርያም ደሳለኝ | የውጭ ጉዳይ ሚንስትር | አባል |
| 3. | አቶ ሲራጅ ፈጌሳ | የሀገር መከላከያ ሚንስትር | አባል |
| 4. | አቶ ሙክታር ከድር | የጠ/ሚንስትሩ ቢሮ ኃላፊ | አባል |
| 5. | አቶ ወርቅነህ ገበየሁ | የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር | አባል |
| 6. | አቶ ሽፈራው ተ/ማርያም | የፌዴራል ጉዳዩች ሚንስትር /ፌ.ጉ.ሚ/ | አባል |
| 7. | አቶ ጌታቸው አሰፋ | የመረጃና ደህንነት ኃላፊ | አባል |
| 8. | አቶ ሪድዋን ሁሴን | የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ጽ/ቤት ኃላፊ | - |

**የእለቱ አጀንዳ:**
ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በህዝበ ሙስሊሙ የተነሳው ተቃውሞ ያለበትን ደረጃ መገምገምና አፋጣኝና ተገቢ ውሳኔዎችን ማሳለፍ::

**መክፈቻ**
ከቡር ጠ/ሚንስትሩ በቅድሚያ የብሄራዊ ደህንነት ምክር ቤት አባላት በሙሉ በአጭር ጥሪ በስብሰባው ላይ ለመገኘት በመቻላቸው ምስጋና በማቅረብ  በቀጥታ ወደ የእለቱ አጀንዳ የገቡ ሲሆን በንግግራቸውም ካለፉት ሰባትና ስምንት ወራት ጀምሮ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ባነሳቸው የሙብት ጥያቄዎችና ተቃውሞ አዲስ አበባን ጨምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ቀላል የማይባል የጸጥታና የመረጋጋት ቀውስ መፈጠሩን፣ መንግስት ችግሩን ለመፍታት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ የቆየ መሆኑንና የተጠበቀው ውጤት አለመገኘቱን፣ መንግስት ችግሩን የተረዳበት አግባብና ችግሩን ለመፍታት የሄደባቸው መንገዶች ሙስሊሙን ማህበረሰብ ለማሳመንና ችግሩን ለመፍታት እንዳልፈየደና ችግሩ ከግዜ ወደ ግዜ እየሰፋና እየተባባሰ መጥቶም አሁን ያለበት ደረጃ ላይ መድረሱን ገልጸዋል:: በማስከተልም ችግሩ በዚሁ ከቀጠለ ወዳልታሰበና ወዳልተጠበቀ አቅጣጫ የመሄድ እድሉ ከፍተኛ መሆኑንና ይህም  ለሀገር ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም መንግስት ለተያያዘው የልማትና የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ከፍተኛ ስጋት ሊሆን እንደሚችል አስረድተዋል::

በመቀጠልም ችግሩን በተመለከተ ባላፉት ጥቂት ወራት የብሄራዊ ደህንነት ምክር ቤት፣ የሚንስትሮች ምክር ቤት፣ የኢህአዴግ ማእከላዊ ኮሚቴና የሚመለከታቸው የመንግስት አካላት በርካታ ውይይቶችን ሲያካሂዱ መቀየታቸውን ጠቅሰው ሆኖም ችግሩን ለመፍታት አለመቻሉን አመልክተዋል:: በመሆኑም የተጀመረው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ሙሉ ለሙሉ ከቁጥጥር ውጭ ከመሆኑ በፊት ችግሩን እንደገና ቆም ብሎ ማየት፣ እስካሁን የተሄደባቸውን አቅጣጫዎችና የተሰሩ ስራዎችን መገምገም፣ የተፈጠሩ የመርህና የአፈጻጸም ግድፈቶች ካሉ ማረምና ለተፈጠረው ቀውስ አፋጣኝ፣ ዘላቂና ስር-ነቀል መፍትሄ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ ሆኖ መገኘቱን ጠቅሰዋል::

አቶ መለስ የስብሰባውን አካሄድ በተመለከተ በቅድሚያ በችግሩ ዙሪያ በግንባር ቀደምትነት እየሰሩ ካሉት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማለትም የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ ፌዴራል ፖሊስና፣ የብሄራዊ የመረጃና የደህንነት አገልግሎት ስለጉዳዩ ማብራሪያዎች ቢሰጡና በቅደም ተከተል ውይይቶችን በማካሄድ ተገቢ የሚባሉ ውሳኔዎች ቢተላለፉ የተሻለ እንደሚሆን የገለጹ ሲሆን በአካሄድ ላይ የተለየ ሀሳብ ካለም ጠይቀዋል:: ተሰብሳቢዎች በስብሰባው አካሄድ ላይ በመስማማታቸው በቀጥታ ወደ አጀንዳው ዝርዝር ጉዳዮች የተገባ ሲሆን  በመጨረሻ ነጥረው የወጡትን የሙስሊሙ ጥያቄዎች አስመልክቶ  ለቀረቡ ጥያቄዎች ዶ/ር ሽፈራው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል:: ከመጀመሪያው ጀምሮ የተነሱት የሙስሊሙ ጥያቄዎች ሶስት መሆናቸውንና እስከ አሁን ድረስ አለመቀየራቸውን ዶ/ር ሽፈራው ገልጸው ጥያቄዎቹም፣

1 አሁን የኢትዮጲያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤትን /መጅሊስ/ በማስተዳደር ያሉ ኃላፊዎች ከኃላፊነታቸው ላይ ተወግደው በምትካቸው በሙስሊሙ ቀጥተኛ ተሳትፎ የተመረጡ ወኪሎች ምክር ቤቱን እንዲረከቡ፣
2 አወሊያ ትምህርት ቤት በቦርድ እንዲተዳደር፣
3 በመካሄድ ላይ ያለው የአህባሽ ስልጠና እንዲቆም መሆናቸውን ገልጸዋል::

በመቀጠል ችግሩን ለመረዳትና ለመፍታት የተሰሩ ስራዎች እንዲገለጹ ክቡር ጠ/ሚንስትሩ ለጠየቁት ጥያቄ ዶ/ር ሽፈራው የሚከተለውን መልሰዋል፡፡ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ስም ጥቂት አክራሪ ግለሰቦችና ቡድኖች ያነሷቸውን ጥያቄዎች ለመመለስ በሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው ከተሰሩት ዋና ዋና ስራዎች መካከል ችግሩን ከመሰረቱ ለመረዳት ብሎም ለጉዳዩ ትክክለኛ መፍትኄ ለመስጠት ይቻል ዘንድ በቅድሚያ ያካሄዱት በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ፈጣን የዳሰሳ ጥናቶችን ማድረግ እንደነበርና በዚህም ረገድ ቀላል የማይባሉ ስራዎች መሰራታቸውን ገልጸዋል፡፡ ዶ/ር ሽፈራው ጥናቶቹን ለማካሄድ ሶስት የተለያዩ የጥናት ግብረኃይሎች የተቋቋሙ መሆኑንና እያንዳንዱ ግብረኃይል ውስን በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ እንዲሰራ መደረጉንን ሁሉም ግብረኃይሎች ስራቸውን ሲያጠናቅቁ ሶስቱንም ጥናቶች ወደ አንድ በማምጣት ችግሩን በተቀናጀ መልኩ ለማየት በሚያስችል መልኩ ሪፖርት መዘጋጀቱንና ሪፖርቱም ለዚሁ ምክር ቤት መቀረቡንና ለሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም መሰራጨቱን አስታውሰዋል፡፡ ጥናቶቹ ሲካሄዱ የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን የተጠሙ መሆናቸውንና ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት መሆናቸውን ገልጸዋል፤

1. በስራ ላይ ካሉ የመጅሊስ አመራር አባላት ጋር የተደረጉ ቃለ-መጠይቅና ውይይቶች፤
2. ሚንስትር መስሪያ ቤቱ ከሊባኖስ ይመጡ ዘንድ ድጋፍ የሰጣቸው የአህባሽ ሊቃውንት፤
3. በተለያዩ የምእራባውያን የፖለቲካና የደህንነት ባለሙያዎች ኢትዮጲያንና የአፍሪካ ቀንድን አስመልክቶ የተጻፉ ጽሁፎች፤
4. ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል ጋር የተደረጉ ህዝባዊ ስብሰባዎች፤
5. ኢስራኤላዊው ሀጋይ ኤርሊች ስለኢትዮጲያ ሙስሊሞች የጻፏቸው መጽሀፍትና አጫጭር ጽሁፎች፤
6. ከአለማቀፍ የመገናኛ ብዙሀን ስለኢስላምና ሙስሊሞች የተወሰዱ መረጃዎች፤
7. ከሌሎች እምነት ተከታዮች አመራር አባላት ጋር የተደረጉ ውይይቶች፤
8. በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች ስለኢስላምና ሙስሊሞች ያላቸውን እውቀት መረጃ መሆናቸውን በቅደም ተከተል አመልክተዋል፡፡

በችግሩ ዙሪያ ከህዝበ ሙስሊሙ ጋር በቀጥታ ለመወያየት የተደረገ ሙከራ መኖሩን አስመልክቶ ለተነሳው ጥያቄ ችግሩ ከተከሰተበት ማግስት ጀምሮ በተለያዩ ደረጃዎች ልዩልዩ ስብሰባዎችና ውይይቶች መካሄዳቸውንና አብዛኛዎቹ ስብሰባዎችም በፌ.ጉ.ሚ፣ በመጅሊሱና በአዲስ አበባ መስተዳድር አማካኝነት የተዘጋጁ መሆናቸው ተገልጧል፡፡ በተፈጠሩት የውይይት መድረኮች ላይ እንዲገኙ ያተደረጉት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመጅሊሱ ዙሪያ የተሰባሰቡ የመጅሊሱ አባላት ወይም ደጋፊዎች እንዲሁም የድርጅት አባላት መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ በተወሰኑ ስብሰባዎች ላይም ተሳታፊዎችን በሚገባ ለመለየት ይቻል ዘንድ የመግቢያ ካርድ የተዘጋጀ ቢሆንም ጥቂት አክራሪ ግለሰቦችና ግብረ አበሮቻቸው ለመሳተፍና የስብሰባውን አቅጣጫ እነሱ በሚፈልጉት አቅጣጫ ለመውሰድ ያልተሳካ ጥረት ማድረጋቸውን ዶ/ር ሽፈራው አብራርተዋል፡፡ በመጨረሻም ከህዝበ ሙስሊሙ ጋር በቀጥታ ለመወያየት የተዘጋጀ መድረክ አለመኖሩንም ገልጸዋል፡፡

**አቶ መለስ ተቃውሞውን ለመፍታት የተወሰዱ ስልቶች እንዲገለጹ በጠየቁት መሰረት ዶ/ር ሽፈራው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡**

በዋናነት የተከተሉት ስልት ሁከቱን በመፍጠር ላይ ያሉትን አክራሪ ግለሰቦችና ቡድኖች ከህዝበ ሙስሊሙ እንዲነጠሉ ማድረግ ብሎም ተቃውሞውን በማካሄድ ላይ ባሉ ሰዎች መካከል ልዩነት በመፍጠር ተቃውሞውን ከውስጥ እንዲዳከም ማድረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የተቃውሞው እንቅስቃሴው ጥቂት ጸረ-ሰላምና ጸረ-ልማት ኃይሎች ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማስፈጸም የፈጠሩትና ሙስሊሙን ህብረተሰብ የማይወክል መሆኑን ለማሳየት ሙከራ መደረጉን ገልጸዋል፡፡ ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ከመንግስት የመገናኛ ብዙሀን ጋር በመተባበር ከፍተኛ የህዝብ ግንኙነት ስራ መሰራቱንና በሙስሊሙ ማህበረሰብና ራሱን "የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ" ብሎ በሚጠራው ቡድን መካከል ልዩነትና ጥርጣሬን ለመፍጠር ልዩ ልዩ ስራዎች መሰራታቸውን አመልክተዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በኮሚቴው አባላት ላይ የስነ-ልቦና ጫና በመፍጠር ከኮሚቴ አባልነታቸው በፍቃደኝነት እንዲወጡ ለማድረግ ጥረት መደረጉንና በየሳምንቱ የአርብ ስግደትን ተከትሎ የሚካሄደውን ተቃውሞ ለማቀዝቀዝ በተደጋጋሚ ልዩ ልዩ መግለጫዎችን በሚኒስትር መስሪያ ቤታቸውና በመጅሊሱ አማካኝነት እንዲሰጡ መደረጉን ዶ/ር ሽፈራው ገልጸዋል፡፡

ዶ/ር ሽፈራው ተቃውሞው የውጭ ኃይሎች እጅ እንዳለበት ለማሳየትም አንዳንድ ስራዎች መሰራታቸው ገልጸው በዚህም ከመጅሊሱ ጋር በመተባበር ከውጭ ሀገር የመጡ ሶስት የውጭ ዜጎች በአንዋር መስጊድ ውስጥ ሙስሊሙን ለአመጽ የሚያነሳሱ ጹሁፎችን ሲበትኑ እንደተያዙና ክሀገር እንዲባረሩ መደረጉን የሚያሳይ ዜና መሰራቱን፣ ስራውም ያለምንም ችግር በተሳካ ሁኔታ መፈጸሙን ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም መንግስት የአክራሪነት አደጋን ለመመከት በማድረግ ላይ ላለው ወሳኝ ትግል የሌሎች እምነት ተከታዮችን በተለይም የህዝበ ክርስቲያኑን ድጋፍ ለማግኘት ይረዳ ዘንድ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የህዝበ ክርስቲያኑን ድጋፍ ለማግኘት የሚየስችሉ ስራዎች መሰራታቸውን አመልክተዋል፡፡ ከላይ የተገለጹትን ስልቶች በመጠቀምና የእንቅስቃሴውን መሪዎች ከህዝቡ ለመነጠል ብሎም የሌላውን ህብረተሰብ ድጋፍ ለማገኘትና ከመንግስት ጎን ለማሰለፍ ያስችላል ተብሎ የታመነበት አንድ ዶኩመንታሪ ፊልም በፖሊስ፣ በደህንነትና በኢቲቪ ትብብር ስራው መጀመሩን ዶ/ር ሽፈራው ገልጸዋል፡፡

**ህዝበ ሙስሊሙ መረጣቸው ስለተባለው "የመፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ" አባላት የፌ.ጉ.ሚ. እንዴት እንደገመገማቸውና ከህዝቡ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ለቀረበው ኃሳብ የሚከተለው ምላሽ ተሰጥቷል፡፡**

ከተባለው ኮሚቴ ጋር ቢያንስ ሁለት ጊዜ ተገናኝተው መወያየታቸውንና አባላቱ የተለያየ እድሜ፤ ሙያና የትምህርት ደረጃ ያላቸው መሆኑን ብሎም በተለያየ የስራ መስኮች የተሰማሩ መሆናቸውን ማለትም ነጋዴ፣ ተማሪ፣ የሀይማኖት ሰባኪ፣ የድርጅት ኃላፊዎች፣ የመስጊድ ኢማሞች፣ ጋዜጠኞች ወዘተ... መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ከኮሚቴው ጋር በተደረገው ግንኙነት የኮሚቴው አባላት በግልም ሆነ

በቡድን በከፍተኛ ሞራልና ስሜት እየሰሩ መሆናቸውን፣ አባላቱ በመግባባትና በከፍተኛ የቡድን ስሜት ስራቸውን በመስራት ላይ እንዳሉ ለመረዳት መቻላቸውን ዶ/ር ሽፈራው ገልጸዋል፡፡በዚህም ምክንያት በኮሚቴው አባላት መካከል ክፍተት ወይም ልዩነት ለመፍጠር የተደረጉ ሙከራዎች ውጤታማ ሊሆኑ አለመቻላቸውን አመልክተዋል፡፡

ኮሚቴው ከህዝቡ ጋር በመተባበር የተጀመረው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ውጤታማ ሆኖ እንዲጠናቀቅ፣ ተቃውሞው ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥልና ወዳልተፈለገ አቅጣጫ በተለይም ወደ አመጽ እንዳይሄድ ሰፊ ስራዎችን በመስራት ላይ እንደሚገኝ ተመልክቷል፡፡ **ኮሚቴው የመጅሊሱንና የመንግስትን እንቅስቃሴ በቅርብ በመከታተል ተገቢ ያላቸውን ውሳኔዎች በጥንቃቄ እንደሚወስድና ተቃውሞውን አስመልክቶ በመንግስትና በመጅሊሱ የሚወጡ መግለጫዎችን ለማምከን በቅንጅት እንደሚሰራ ዶ/ር ሽፈራው ገልጸዋል፡** ፡ ኮሚቴው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ሰፊ ኔትወርክ መመስረት መቻሉንና ሰፊ የህዝብ ተቀባይነት እንዳገኘ ለማረጋገጥ መቻላቸውንም ዶ/ር ሽፈራው አመልክተው በተለይም በሀገር ውስጥ ዋና አመራሩ አዲስ አበባ ላይ ሆኖ በሁሉም ክልሎች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች እስከ መስጊድ/መንደር የሚደርስ ሰንሰለት ለመዘርጋት መቻሉንና ይህ አደረጃጀትም ኮሚቴው በየጊዜው የሚያወጣቸው መግለጫዎችና ትእዛዞች በመላ የሀገሪቱ ክፍል በፍጥነት እንዲደርሱ ምቹ ሁኔታ የፈጠረለት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ግንቦት 3 ቀን በተለይ በአንዋር መስጊድ በተከበረው የአርብ ስግደት ምእመናኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ያለድምጽ /አላሁከበር ሳይባል/ በጸጥታ እንዲያከብሩ ኮሚቴው የሰጠው ትእዛዝ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሆኗል ብለዋል፡፡

**ችግሩን አባብሰዋል ወይም ሊያባብሱ ይችላሉ ተብለው የተለዩ ጉዳዮች ለማየት የተደረገ ሙከራ ካለ መግለጫ እንዲሰጥ ለቀረበው ጥያቄ የሚከተለው መልስ ተሰጥቷል፡፡**

ጉዳዩ ሀይማኖታዊ በመሆኑ ቶሎ ለመስፋፋት ሌላ አጋዥ ሁኔታዎችን እንደማይፈልግና በራሱ ከበቂ በላይ ምክንያት መሆኑን ዶ/ር ሽፈራው ገልጸዋል፡፡ በተለይ አንዳንድ ጽንፈኛ ሙስሊሞች ኢትዮጲያውያን ሙስሊሞች ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ብዙ ጭቆናና የሙብት ረገጣ አለብን ብለው ህዝቡን ለማደናገር እንደሚጥሩ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ ችግር ጋር ሊያያዝ ይችላል ተብሎ የሚታመን በመረጃ የተደገፍ ምንም ጉዳይ አለመኖሩንና ሆኖም በአንድ ወቅት ሰፊ የመነጋገሪያ አጀንዳ የነበረው የዘምዘም ባንክ የምስረታ ሂደት መቋረጥ የራሱ የሆነ አስተዋጾ ሊኖረው ይችላል ብለው በግላቸው እንደሚያምኑ ዶ/ር ሽፈራው ገልጸዋል፡፡

ባንኩን አስመልክቶ ዶ/ር ሽፈራው በሰጡት ተጨማሪ ማብራሪያ የዘምዘም ባንክ የምስረታ ሂደት ኢትዮጲያ ውስጥ የግል ባንኮችን ለማቋቋም ባማካኝ ከሚወስደው ጊዜ አንጻር ረጅም ሊባል የሚችል ጊዜ መውሰዱን፣ በኢትዮጲያ ውስጥ ወለድ አልባ የገንዘብ ተቋማትን ማቋቋም እንደሚቻል የሚፈቅደው የባንክ ስራ አዋጅ ከወጣና ሌሎች አስፈላጊ ህጋዊና ቴክኒካዊ ዝግጅቶች ከተጠናቀቁና የዘምዘም ባንክ ሁሉንም ቅድመ ዝግጅቶች አጠናቆ የአክስዮን ሽያጭ ካካሄደ በኃላ ባንኩን መክፈት እንደማይቻል በብሄራዊ ባንክ መታገዱን ተናግረዋል፡፡ በብሄራዊ ባንኩ የተሰጠውም ምክንያት ለህዝቡ አሳማኝ እንዳልነበረና ግልጽነት የሚጎለው እንደነበረ ዶ/ር ሽፈራው አመልክተው ባንኩን ለማስቆም የተወሰደው እርምጃም ሙስሊሙን ህብረተሰብ በኢኮኖሚ ለማዳከም ታስቦ የተደረገ እንደሆነ በአክራሪዎቹ በስፋት መስተጋባቱን፣ ይህም በአብዛኛው ሙስሊም ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱንና የአብዛኛውን ሙስሊም ህብረተሰብ ስሜት መጉዳቱን፣ ይህ ቁርሾ ባለበት ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱት ሀይማኖታዊ ችግሮች ሲከሰቱ ችግሩን የበለጠ ውስብስብ ሊያደርጉት እንደቻሉ ዶ/ር ሽፈራው ግምታቸውን ተናግረዋል፡፡

በመቀጠልም የዋልድባ ገዳም ጉዳይ አንደ አንድ ጉዳይ ሊጠቀስ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ የገዳሙ መፍረስ በተለየም በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ ከፍተኛ ቁጣን ማስነሳቱና ይህም መንግስት በአጠቃላይ በሁሉም ሀይማኖቶች ጉዳይ ላይ ጣልቃ እየገባ እንደሆነ ለማሳየትና በሙስሊሞች የተጀመረውን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ምቹ ሁኔታዎች መፍጠሩ ተወስቷል፡፡ ይህ ጉዳይ በተለይ የክርስቲያኑን ማህበረሰብ ድጋፍ ለማገኘት የተደረገውን እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዳይሆን የራሱ የሆነ አስተዋጾ እንዳለውና ከዚህም አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በጋራ በመሆን ተቃውሞ እንዲያደርጉና ችግሩ እንዲባባስ ከፍተኛ አስተዋጾ ማድረጉ ተወስቷል፡፡ በዋሽንግተንና በሌሎች የአውሮፓ ከተሞች የተደረጉ የጋራ የተቀውሞ ሰልፎች እንደምሳሌ ቀርበዋል ፡፡

**በመቀጠል በችግሩ ዙሪያ የፖሊስን እንቅስቀሴና ሚና አስመልክቶ መግለጫ እንዲቀርብ ክቡር ጠ/ሚንስትሩ በጠየቁት መሰረት አቶ ወርቅነህ የሚከተለውን ብለዋል፡፡**

ችግሩ ከተከሰተበት ግዜ ጀምሮ የፌደራልና የክልል ፖሊስ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር እየሰሩ እንደሚገኙና ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ዋናዋና ስራዎች እንደሚገኙበት አመልክተዋል፤

- ዘወትር አርብ በተለይ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ሙስሊም በሚሰበሰብባቸው መስጊዶች ማለትም በአወሊያ መስጊድ /ዊንጌት/፣ አንዋር መስጊድ /መርካቶ/ እና በበኒ መስጊድ /ፒያሳ/ አካባቢ ብዛት ያላቸው ፖሊስ አባላትን በማሰለፍ ጸጥታን የማስከበር ስራ ተሰርቷል፡፡ ለዚህም ስራ ይረዳ ዘንድ አድማ በታኝ ልዩ ኃይል ከነሙሉ ትጥቅ /ማለትም አስለቃሽ ጋዝ፣ የውሀ መርጫ ተሽከርካሪዎች፣ የሰለጠኑ ውሾች ወዘተ.../ መሰማራቱን፣
- ጥንቃቄ በተመላበት ሁኔታ ሙስሊሞች በተለይ ከነዚህ ከላይ ከተጠቀሱት መስጊዶች አካባቢ እንዲርቁ የሚያስችሉ ስራዎች መሰራቱን፣
- በምስራቅ አርሲ አሳሳ ከተማ ላይ ለረዥርም ጊዜ በመንግስት ይፈለጉ የነበሩ ጽንፈኞችን ለማስወገድ ይቻል ዘንድ በአንድ የከተማው መስጊድ ውስጥ በተሰራ የተቀናጀ ኦፕሬሽን ለረጅም ጊዜ ለመንግስት ስጋት ሆነው የቆዩ ጥቂት ሰዎች እንዲወገዱ ተደርጓል፡፡ በርከት ያሉ ግብረ አበሮቻቸውም መታሰራቸው ተገልጧል፡፡

በሂደቱ በፖሊስ አባላት እና በንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት እንዲገለጽ ለተጠየቀው ጥያቄ አቶ ወርቅነህ መልስ የሰጡ ሲሆን በዚህም ምንም አይነት ጉዳት አለመፈጠሩን አመልክተዋል፡፡ አቶ ወርቅነህ ህዝቡ እጅግ በሰለጠነና ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ተቃውሞውን በተለያየ መንገድ ከገነጸ በኃላ ወደቤቱ በሰላም እንደሚመለስ አመልክተው የተቃውሞ ሂዳቱ ሞዴል ሊባል የሚችል ለሀገራችን አዲስ ባህል እንደሆን ገልጸዋል፡፡ አቶ ወርቅነህ በመቀጠል በተለያየ ወቅትና አጋጣሚ በመንግስት በተሰጡ መግለጫዎች በፖሊስ አባላትና ንብረት እንዲሁም በህዝብና በመንግስት ሀብት ላይ አንዳንድ ጥቃቶች እየተፈጸሙ እንደሆነና መንግስት እርምጃ እንደሚወስድ የተጠቀሰ ቢሆንም ይህ ባጠቃልይ ተቃውሞውን ለማብረድና በተቃዋሚዎች ላይ የስነልቦና ጫና ለመፍጠር መንግስት እየተከተለ ካለው ስትራቴጂ አንጻር የተሰራ እንጂ በእርግጥ በፖሊስ አባላትም ሆነ ንብረት እንዲሁም በህዝብና በመንግስት ላይ የተፈጠረ ምንም አይነት ጉዳት እንደሌለ አቶ ወርቅነህ አመልክተዋል፡፡

የመፍትሄ አፈላላጊ የተሰኘው ኮሚቴ  አንዳንድ አባላት ድብቅ የፖለቲካ አጀንዳ እንዳላቸው ለተላለፈው መልእክት በፖሊስ በኩል ስለተገኘ ተጨባጭ መረጃ መብራሪያ እንዲሰጥበት ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረበው ጥያቄ አቶ ወርቅነህ መልስ የሰጡ ሲሆን ፖሊስ ጉዳዩን በተጨባጭ ለማረጋገጥ የሚያስችል ምንም አይነት የጽሁፍ፣ የድምጽ ወይም የምስል መረጃ ለማግኘት እንዳልቻለና ስራው ተጠናክሮ እየተሰራ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ይህ ጉዳይ በሚዲያ ላይ በተደጋጋሚ እንዲቀርብ የተደገረገበት ዋናው ምክንያት ከላይ እንደተገለጸው በኮሚቴው አባላትና ለተቃውሞ በሚወጣው ህዝብ ላይ የስነልቦና ጫና በማንገስ ተቃውሞውን ለማርገብና ለመፈረካከስ ሁሉም የመንግስተ አካላት ከሚከተሉት አጠቃላይ ስልት አንጻር ታስቦ መሆኑን አቶ ወርቅነህ አብራርተዋል፡፡

**ተቃውሞው በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ውስጥ ያስከተለውን ችግርና የፈጠረውን አንድምታ፣ በቀጣይ ምርጫዎች ላይ ሊኖረው የሚችለውን ተጽኖ እንዲሁም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ችግሩን ሊጠቀሙበት የሚችሉበትን አግባብ በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ለቀረበው ሀሳብ አቶ ሪድዋን የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡**
ችግሩ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ውስጥ ከፍተኛ ነውጥ መፍጠሩንና ጉዳዩ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. አባላት መካከል ከፍተኛ ክፍፍል እንዲፈጠር ምክንያት መሆኑን አመልክተዋል፡፡በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያሉ አመራሮች ሳይቀሩ በተፈጠረው ችግሩ ዙሪያ ግልጽ ወገንተኝነት ያሳዩበት ሁኔታ መከሰቱንና ቁጥሩ ከፍተኛ ሊባል የሚችል የድርጅት አባል በተለይም ሙስሊም አባላት በጉዳዩ ላይ ያላቸው አቋም ሀይማኖታቸውን መሰረት ያደረገ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል፡፡ በተለይ ሙስሊም የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. አባላት ከተራው ህዝብ ባልተናነሰ ሁኔታ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. እና የመንግስትን አቋም በይፋ መቃወም ብቻ ሳይሆን መንግስትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ከችግሩ ውስት እጃቸውን በአፋጣኝ ካላወጡ አባልነታቸውን በገዛ ፈቃዳቸው ለመልቀቅ የዛቱ ጥቂት እንዳልሆኑ አቶ ሪድዋን ገልጸዋል፡፡በአጠቃልይ እንደ ድርጅት ሳይሆን እንደሀይማኖት ማሰብ መጀመሩንና ቀላል የማይባሉ የክርስትና እምነት ተከታይ አባላት ሳይቀሩ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር የተፈጠረውን ችግር ከክርስትና እምነት ተከታዮች ጋር በተለያዩ ጊዜያት ከተፈጠሩት ችግሮች ጋር በማያያዝ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ላይ የሰላ ትችት በማቅረብ ላይ እንደሚገኙ በስፋት ተገልጧል፡፡

በችግሩ ዙሪያ ድርጅታዊ መግባባትን ለመፍጠር ይረዳ ዘንድ አንድ ባለ 25 ገጽ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለአባላት ለውይይት መቅረቡን አቶ ሬድዋን የገለጹ ሲሆን ሰነዱ "**በእምነት ነጻነትና በህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎቻችን ዙሪያ ግልጽነት በመፍጠር ጸረ-ልማትና ጸረ-ዴሞክራሲ የሆነውን አክራሪነት በዘላቂነት የመዋጋት አስፈላጊነትና ተልእኮዎቻችን**" በሚል ርእስ የተዘጋጀ መሆኑንና ሰነዱ የአክራሪነት አደጋን በአብዛኛው ከእስልምና ጋር አልፎ አልፎም ከክርስትና የተለያዩ ሴክቶች ጋር በማያያዝ ለማሳየት እንደሚሞክር አቶ ሬድዋን አስረድተዋል፡፡ ይህንኑ ሰነድ መነሻ በማድረግ በተዋረድ ከክልል እስከ ቀበሌ ባለው መዋቅር እስከ ህዋስ የሚዘልቅ የድርጊት መርሀግብር ተዘጋጅቶ ወደስራ የተገባበት ሁኔታዎች መኖራቸውንና ሆኖም ችግሩ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ውስጥ ከፍተኛ ከፍተት መፍጠሩንና ይህ ሁኔታም በኢህአዴግ  ድርጅታዊ ጥንካሬ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽኖ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል አቶ ሬድዋን ጠቁመዋ፡፡

ችግሩ በ2005ቱ የአካባቢ ምርጫና እና በ2007 ከሚካሄደው አጠቃላይ ሀገራዊ ምርጫ አንጻር የሚኖረውን እንድምታ አስመልክቶ ለቀረበው ሀሳብ አቶ ሬድዋን ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን ከዚህ አንጻር ብዙ የተሰራ ስራ እንደሌለና ለዚህም ዋና ምክንያት የምርጫዎቹ ግዜ ትንሽ መራቅ ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል፡፡ ይሁን እንጅ ከሙስሊሙ ጋር የተፈጠረው ችግር በቀጣይ በሚካሄዱ ማንኛውም አይነት ምርጫዎች በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ላይ አሉታዊ ተጽኖ ሊፈጥር እንደሚችል መገመት እንደሚቻል አቶ ሬድዋን ያመለከቱ ሲሆን ጉዳዩ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ተነስቶ ውይይት የተደረገበት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ አንዳንድ የድርጅት አባላት ከሙስሊሙ ጋር የተፈጠረው አለመግባባት በቀጣይ ምርጫዎች ላይ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል አበክረው የገለጹበት ሁኔታ መኖሩንና ከዚህ በፊት በተካሄዱ የብሄራዊ፣ የክልልና የአካባቢ ምርጫዎች ላይ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. የሰጠው ድጋፍ ምትክ የሌለው እንደነበር አውስተዋል፡፡ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. በተለይ ሙስሊሞች በሚበዙባቸው ክልሎችና አካባቢዎች በተለያዩ የምርጫ አጋጣሚዎች የሙስሊሙን ታሪካዊ ሁኔታና በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. የተጎናጸፋቸውን የእምነት ነጻነት በማስታወስ ያካሄደው ቅስቀሳና የተከተለው የምርጫ ስልት ውጤታማ እንደነበርም ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም በተለይም በ1997 ሀገር አቀፍ ምርጫ ጋ በተያያዘ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ካጋጠመው ችግር እንዲወጣ ሙስሊሙ ህብረተሰብና ሙስሊም ክልሎች ከፍተኛ እገዛ እንዳደረጉ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ከፍተኛ አመራር እንደሚያምን ገልጸዋል፡፡

በመቀጠል ተቃዋሚ ድርጅቶች የተፈጠረውን ክስተት ለመጠቀም ያደረጉትን እንቅስቃሴና ያገኙትን ውጤት በተመለከተ አቶ ሬድዋን ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን በውጭ የሚገኙ አንዳንድ የተቃዋሚ ድርጅቶች ኃላፊዎች መንግስት ከሙስሊሙ ጋር የፈጠረውን ችግል ለመጠቀም አንዳንድ ሙከራዎች ማድረጋቸውን፣ በተለይም በአውሮፓና በአሜሪካ የሚገኙ ተቃዋሚ ድርጅቶች በአጋጣሚው ለመጠቀም በስፋት እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡ ሆኖም ግን በውጤቱ ብዙ እንዳልተሳካላቸውና አብዛኛው ሙስሊም ህብረተሰብ ለተቃዋሚ ድርጅቶች ያለው አመለካከት ፖዘቲቭ እንዳልሆነ አቶ ሬድዋን አመልክተዋል፡፡ ቁጥሩ ከፍተኛ ሊባል የሚችል የሙስሊሙ ማህበረሰብ ተቃዋሚ ድርጅቶችን ያለፉት አሀዳዊ ስርአቶች አቀንቃኞችና ናፋቂዎች እንዲሁም በሃይማኖት አኩልነት

የማያምኑ አድርጎ እንደሚያስብና በዚህም አንጻር ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. በተለያዩ አጋጣሚዎች የሰራቸው የፕሮፓጋንዳ ስራዎች ከፍተኛ ውጤት ሳያስገኙ እንዳልቀሩ አቶ ሬድዋን አመልክተዋል፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ አቶ ሬድዋን በቅርቡ ያነበቡትን ጽሁፍን ዋቢ አድርገው ሲናገሩ በተለይም አሁን ሙስሊሙ ከመንግስት ጋር በተፈጠረው ችግር ዙሪያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ያሳዩት ለዘብተኝነት አብዛኛውን ሙስሊም እንዳሳዘነው የሚጠቅስ መሆኑንና ሙስሊሙ የራሱ የሆነ ጠንካራ የፖለቲካ አቅም መፍጠር እስኪችል ድረስ ከተቃዋሚ ድርጅቶች ይልቅ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ.ን እየመከረና እያረቀ መሄድ እንደሚሻል ይመክራል ብለዋል፡፡ እስካሁን ባለው ሁኔታ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከችግሩ ብዙ ያተርፋሉ ብለው እንደማይሰጉ፣ ይሁን እንጂ ችግሩ በተቻለ ፍጥነት መፍትሄ ካላገኘ በቀጣይ በሚካሄዱ ሀገራዊ ምርጫዎች ላይ ሙስሊሙ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ከመቅጣት ወደ ኋላ እንደማይልና ይህም በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ቀጣይ ጉዞ ላይ ቀላል ሊባል የማይችል አደጋ ሊፈጥር እንደሚችል ያላቸውን ስጋት አበክረው ገልጸዋል፡፡ በመጨረሻም ከሙስሊሙ ጋር የተፈጠረውን ችግር ከምርጫ ማሸነፍና መሸነፍ ጋር ብቻ ማየት ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ዴሞክራሲያዊ ባህል ጋር እንደሚጋጭና ሙስሊሙ ያነሳቸው ጥያቄዎች ፍትህዊ ናቸው ተብለው ከታመነባቸው ጥያቄዎቹን ባፋጣኝ መፍታት እንደሚያስፈልግ በመግለጽ አቶ ሬድዋን ኃሳባቸውን አጠቃለዋል፡፡

**ችግሩን ከመፍታት አንጻር በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር አስመልክቶ አጠር ያለ ማብራሪያ ቢሰጥ ሲሉ አቶ ሙክታር ለቀረቡት ጥያቄ ዶ/ር ሽፈራው የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፡፡**

በፌደራል ጉዳዮች ሰብሳቢነት የሚሰራው ልዩ ኮሚቴ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ ስራዎችን በበላይነት የሚያስተባብር ሲሆን ከፍተኛ ውሳኔ የሚሹ ጉዳዩችን ለበላይ አካል በማቅረብ ውሳኔ እንዲሰጥባቸው እንደሚደረግ ገልጸው በኮሚቴው ውስጥ የመጅሊሱን ተወካዮች ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸው የፌዴራል መስሪያ ቤቶች በአባልነት እንደሚሰሩና የቅንጅት ስራው በአጠቃላይ ሲታይ ጥሩ ሊባል የሚችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. እና በመንግስት ከፍተኛ አመራር ዘንድ የጠራ አቋምና የጋራ መግባባት ይኖር ዘንድ አሁን ያለው የእስልምና ጉዳይ ምክር ቤት ወይም መጅሊስ በስልጣን ላይ እንዲቆይ ለምን እንደተፈለገ በቂ ማብራሪያ እንዲሰጥበት በአቶ ሙክታር ለቀረበው ጥያቄ አቶ ጌታቸውና አቶ ሽፈራው በየተራ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በዚህም አሁን መጅሊሱን በመምራ ላይ የሚገኙት ኃላፊዎች ከሰባት ወይም ስምንት ዓመታት በፊት በደህንነት በኩል በጥንቃቄ ተመርጠው የተቀመጡ መሆናቸውና ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. እና ለመንግስት ፍጹም ታማኝ መሆናቸው ተመልክቷል፡፡ አሁን ያሉት ሰዎች በስልጣን ላይ በመቆየታቸው ምክንያት መንግስትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. በብዙ መንገድ የተጠቀሙ መሆናቸው የተገለጸ ሲሆን ዋና ዋናዎች፤

i. የጠለቀ ሐይማኖታዊ እውቀት እና በቂ የአካዳሚክ ትምህርት የሌላቸው በመሆኑ ከሙስሊሙ ጋር በተገናኘ መንግስትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. የፈለጉትን መመሪያና ፕሮግራሞች ያለምንም ችግር ለማሰራት መቻሉ፤

ii. አብዛኞቹ የመጅሊሱ አባላት በሙስና የተዘፈቁ መሆናቸውና ይህንን የሙስራ ተግባራቸውን በተመለከተ መንግስት በቂ መረጃ እንዳለው ራሳቸው የመጅሊሱ አባላት ማወቃቸው የመጅሊሱ አመራር አባላት ከተጠያቂነት ለመዳንና የመንግስን ከለላ ለማገኘት ፍጹም ታዛኘ ሆነው መገኘታቸው፤ ከዚህ አንጻር ከሀጅና ኡምራ እንዲሁም ከሌሎች ልዩ ልዩ ምንጮች የሚገኙ ከፍተኛ የመጅሊሱ ገንዘብ ለከፍተኛ ሙስና የተጋለጠ መሆኑ ተገልጧል፤

iii. ሙስሊሙን በተመለከተ መንግስት አልፎ አልፎ ለሚያወጣቸው መመሪያዎች (ለምሳሌ በትምህርት ተቋማት ሰላት መስገድን መከልከል፤ ሙስሊም ሴት ተማሪዎችን በትምህርት ቤት ሂጃብ መከልከል..ወዘተ ) አስመልክቶ ለመንግስት ሙሉ ድጋፍ ማድረጋቸው፤ በዚህም የሙስሊሙ ተቃውሞ ወደ መንግስት መሆኑ ቀርቶ በመጅሊሱ ላይ እንዲያርፍ ለመንግስት ከፍተኛ ሽፍን መሆናቸው፤

iv. የማስፈጸም አቅማችው እጅግ ውስን በመሆኑ ከአረቡና ከሙስሊሙ አለም ጋር በሀይማኖታዊም ይሁን በልማት ዙሪያ ያላቸው ግንኙነትና ትብብር ደካማ መሆኑና ይህ ሁኔታም እንደሀገር ከአረቡና ከሙስሊሙ አለም በኩል ሊፈጠር የሚችልን ስጋት ከመቀነስ አንጻር እጅግ አስፈላጊ መሆኑ፣ የኢትዮጲያ ሙስሊሞች በተለይ ከሱዳንና ግብጽ እንዲሁም ከሌሎች የአረብ ሀገራት ጋር የሚፈጥሩት ግንኙነት ለኢትዮጲያ ሰላምና ጸጥታ አደጋ ሊሆን መቻሉ፣

v. ባለፉት 20 ዓመታት የሙስሊሙ የትምህርት ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ ከመጨመሩ አንጻር ጠንካራ እንዲሁም በሀገር ውስጥ እና በውጭ ተቀባይነት ያለው መጅሊስ ቢኖር የፌደራልና የክልል መንግስታት ለትምህርት ሴክተሩ ከሚመድቡት በጀት ያልተናነሰ ሀብት በማሰባሰብ የሙስሊሙን የትምህርት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ መቻሉ፣ ይህም የሙስሊሙን አጠቃላይ እድገት እንደሚያፋጥን፣ ይህ ሁኔታም በሀገርም ሆነ በአፍሪካ ቀንድ ሊፈጥር የሚችለውን የኃይል ሚዝን የማዛባት አደጋ በተለያዩ ሀገራዊና አካባቢያዊ የደህንነት ስብሰባዎች ላይ ጠለቅ ያለ ውይይቶች ተካሂደው አቋም የተወሰደበት ጉዳይ መሆኑን ዶ/ር ሽፈራው በስፋት አብራርተዋል፡፡

ከዚህ አንጻር በህዝበ ሙስሊሙ ሙሉ ተሳትፎ አዲስ መጅሊስ ቢቋቋም ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ.ም ሆነ ለመንግስት ሊፈጥር የሚችለው አደጋ ምን ሊሆን እንደሚችል ለቀረበው ጥያቄ ዶ/ር ሽፈራው በሰጡት ማብራሪያ ባለፉት ሁለት አስርተ አመታት ሙስሊሙ ማህበረሰብ እንደማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ የተሻለ የትምህርትና ስልጠና እድል ማግኘቱና በተፈጠረው አንጻራዊ የሀይማኖት ነጻነትም የሙስሊሞች ሀይማኖታዊ እውቀት በከፍተኛ ሁኔታ ማደጉን አመልክተው በዚህም ሳቢያ የሙስሊሙን መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ህይወት በአጭር ግዜ ለመለወጥ የሚችሉ መሪዎች መፈጠራቸውን፣ በዚህ ሁኔታ ሙስሊሙ መሪዎቹን ነጻና ፍትህዊ በሆነ ሁኔታ እንዲመርጥ እድል ቢሰጠው በኃላፊነት የሚመጡት አመራሮች፤

- በአካዳሚና በመንፈሳዊ እውቀት የተገነቡ፣
- የዳበረ የስራ ልምድ ያላቸው፣
- በሙስሊሙና በአረቡ አለም ውስጥ ሰፊ ኔትዎርክ ያላቸውና በቅርበት መስራት የሚችሉ፣
- ከፍተኛ የህዝብ አመኔታ ያላቸው፣
- ከመንግስት በኩል የሚሰጣቸውን መመሪያ ለመቀበል ዝግጁ ያልሆኑ ምናልባትም በተቃራኒ ሊሰሩ የሚችሉ እንደሚሆኑ ዶ/ር ሽፈራው የግል እምነታቸውን ሰጥተዋል፡፡

**ከችግሩ ጋር ተያይዞ በመንግስት በኩል የአክራሪነት መገለጫዎች የሚባሉትን መመዘኛዎች በተመለከተ ማብራሪያ እንዲሰጥባቸው ለቀረበው ጥያቄ  በመንግስት በኩል የተወሰዱ ዋና ዋና የአክራሪነት መገለጫዎች የሚከተሉት መሆናቸው ተመልክቷል፤**

1 ለመንግስት ግብር መክፈል ከልክልነው ብለው የሚያስተምሩ፣
2 የባንክ ወለድ መውሰድ ወይም መቀበል ሀራም ነው ብለው የሚያስተምሩ፣
3 በትምህርት ተቋማት ውስጥ ሰላት መስገጃ ቦታ እንዲሰጥ የሚጠይቁና በቀን አምስት ግዜና ከዚያም በላይ ሰላት የሚሰግዱ፤
4 ሂጃብና ኒቃብ የሚለብሱ ሴቶች፤
5 በተለየ ሁኔታ ጺማቸውን የሚያስረዝሙና፣ ሱሪ የሚያሳጥሩ፣
6 አሁን ያለው የመጅሊስ አመራር እንዲቀየርና ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ እንዲካሄድ የሚጠይቁ፤
7 የኢትዮጲያ ሙስሊሞች በታሪክ የደረሰባቸውን በደል በማስታወስ ሙስሊሙን ለበቀል የሚያነሳሱ፤
8 መጠጥ በሚስተናገድበት ጠረጴዛዎች ላይ ለስብሰባ ወይም ለምግብ አንቀመጥም ብለው አሻፈረን የሚሉ፤
9 በተለያዩ የስልጠና ቦታዎች የሙስሊም ምግብ ይዘጋጅ ብለው አምቧጓሮ የሚፈጥሩ፣
10 በየመስጊዱ፣ በየሰፈሩና በየቤቱ እተዘዋወሩ ኢስላማዊ ትምህርት የሚያስተምሩ፤

እነዚህ ዋና ዋና የኢስላም አክራሪነት መገለጫዎች ተደርገው እንደሚወሰዱ እና ይሁን እንጂ እነዚህን ሁሉ መገለጫዎች በግርድፉ ወስዶ ለመተግበር እንደሚያስቸግር ተመልክቷል፡፡

**በማስከተል በችግሩ ዙሪያ በመረጃና ደህንነት መስሪያ ቤት የተሰሩ ዋና ዋና ስራዎችንና የተገኙ ውጤቶችን በተመለከተ አቶ ጌታቸው ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡**

ከውስጥና ከውጭ ሊፈጠሩ የሚችሉ አደጋዎችን በመከታተል በሀገርና በህዝብ ላይ አደጋ ከመድረሱ በፊት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ድጋፍ ማድረግ የደህንነት መዋቅሩ ዋና ተልእኮ እንደሆነ የገለጹት አቶ ጌታቸው ከሀገራችን ወቅታዊ የሙስሊሙ ህብረተሰብ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ የመረጃና ደህንነት መስሪያ ቤት ከፌደራል ጉዳዮችና ከሌሎች የሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት ጋር በቅርበት እየሰራ መሆኑንና ስራዎቹንም በሚከተሉት ዋናዋና ክፍሎች ከፍሎ ማየት እንደሚቻል አመልክተዋል፣

1. ከተቃውሞው ጋር ጠንካራ ግንኑነት አላቸው ተብሎ የሚጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ ልዩ ትኩረት  በማድረግ በአካልና በተለያዩ መንገዶች ክትትል ማድረግ፣
2. ከተቃውሞው ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦችና ድርጅቶች እንቅስቃሴ በተለያየ መንገድ መከታተል፣ የሞባይል መስመሮችን መጥለፍ፣ የተጠርጣሪ ግለሰቦችን ኢ-ሜይሎች መስበርና መረጃ ማሰባሰብ፣ የፌስቡክና የፓል ቶክ መልእክቶችን መከታተል፣ መተንተንና አደጋን መተንበይ፣
3. ተቃውሞው ምናልባት ከውጭ ኃይላት ጋር ሊኖረው የሚችለውን ግንኙነት ለማግኘት መረጃዎችን መፈለግና መተንተን መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡
4. በሀገር ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ የአረብና ሙስሊም ሀገራት ዜጎችን /ዲፕሎማቶችን ጨምሮ/ መከታተልና በሀገር ውስጥ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴና ግንኙነት በቅርብ መከታተል፣

አቶ ጌታቸው እስከአሁን የተሰሩ ስራዎችንና ውጤቱን በግላቸው እንዴት እንደሚገመግሙ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ እየተደረገ ካለው መጠነ ሰፊ እንቅስቃሴ አንጻር የተገኘው ውጤት አጥጋቢ እንዳልሆነና ጉዳዩን ወደፍርድ ለማቅረብ በደህንነትም ሆነ በፖሊስ የተሰበሰቡ መረጃዎች እጅግ አናሳ መሆናቸውን አስምረውበታል፡፡ በቀጣይ የተሻለ መረጃ ለማሰባሰብ ይቻል ዘንድ ከእስካሁኑ የተለየ ስልት ለመከተል እንደታሰበ፣ አዲሱ አካሄድም የተሻለ መረጃ ለማግኘት እንደሚያስችልና ዝርዝሩን በሌላ ጊዜ እንደሚቀርቡ አመልክተዋል፡፡ አቶ ጌታቸው የደህንነት መዋቅሩ በጉዳዩ ላይ ያለውን የባለቤትነት ድርሻ ሲያብራሩ ጉዳዩ ምንም እንኳን በፌዴራል ጉዳዮች አስተባባሪነት የሚሰራ ቢሆንም ከጥቂት አስተዳደራዊ ጉዳዮች ውጭ ስራው ሙሉ ለሙሉ በደህንነት መዋቅሩ እየተሰራ ያለ መሆኑንና ለዚህም ዋናው ምክንያት ችግሩ ከሀገር ደህንነት ጋር ያለው ከፍተኛ ቁርኝትና ስራው የሚፈልገው ከፍተኛ ሚስጥር  መሆኑን ገልጸዋል፡፡

**ችግሩ ከውጭ ግንኙነት ጋር በተያያዘ የፈጠረውን ተጽኖ በተመለከተ ለቀረቡ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች አቶ ሀይለማርያም መልስ ሰጥተዋል፡፡**

አቶ ሀይለማርያም የሙስሊሙ ጥያቄ ያልነካካው ሴክተር እንደሌለና ጉዳዩ በውጭ ግንኙነታችንም ላይ ቀላል የማይባል ጫና መፍጠሩን በማመልከት ከውጭ ግንኙነት ጋር በተያያዘ በተለይ ከሙስሊሙ እና ከአረቡ አለም ወዳጆቻችን ጋር በነበረው ግንኙነት ላይ የራሱ የሆነ አሉታዊ ተጽኖ መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡ አቶ ሀይለማርያም በተለይ አንዳንድ መንግስታት በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አቋም

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለመግለጽ የሞከሩባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ በማመልከት ከውጭ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ ሁነቶችንና የተሰሩ ስራዎችን በዝርዝር ያብራሩ ሲሆን እነሱም ፤

- አንድ የአረብ ሀገር አምባሳደሩን ወደ ሀገሩ መጥራቱን፣
- ሶስት ሀገራት በችግሩ ዙሪያ ማብራሪያ እንዲሰጣቸው ለውጭ ጉዳይ ጥያቄ ማቅረባቸውን፣
- በተለያዩ ሀገራት ያሉ ሁለት አማባሳደሮቻችን ባሉበት ሀገር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ተጠርተው ስለጉዳዩ ማብራሪያ እንዲሰጡ በተጠየቁት መሰረት መስፈላጊውን ማብራሪያ መስጠታቸውን፣
- የሚንስቴር መስሪያ ቤቱ የመካከለኛው ምስራቅ ዳይሬክቶሬት በጉዳዩ ላይ የተሻለ ግንዛቤ ለመፍጠር አዲስ አበባ ላይ አንድ የውይይት መድረክ ያዘጋጀ መሆኑንና በዚህም ውይይት ከሃያ የማያንሱ የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት አምባሳደሮችና ከፍተኛ ኃላፊዎች እንዲሁም ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሆኑ የአለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች መገኘታቸውን፤ በውይይቱም ላይ በሀገራችን የተፈጠረው ችግር በተለይም በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ እያደገ በመምጣት ላይ ካለው የአሸባሪነትና የአክራሪነት አደጋ አካል መሆኑን ለማሳየት ጥረት መደረጉን፣
- በካርቱም፤ በካይሮ፤ በአውሮፓና አሜሪካ የተለያዩ ከተሞች እንዲሁም በሌሎች ሀገራት ልዩ ልዩ ሰላማዊ ሰልፎች መካሄዳቸውንና ኤምባሲዎቻችን ባሉበት ሀገራት የተቃውሞ ደብዳቤዎች ለአምባሳደሮቻችን መስጠቱን፣
- በተለያዩ ሀገር በማገልገል ላይ ካሉ አምባሳደሮቻችን ጋር በስልክና በአካል በመገናኘት ስለጉዳዩ ሰፊ ውይይት መደረጉንና በተለይ ሙስሊም አምባሳደሮቻችን በጉዳዩ ላይ መንግስት ያለውን አቋም አስመልክቶ በግል ስጋት እንዳደረባቸው ለመረዳት መቻሉን ገልጸዋል፡፡ አቶ ኃይለማርያም በተለይ ሶስት አማባሳደሮች ማለትም አምባሳደር ሀሰን አብደላ /የመን/ አምባሳደር ማህሙድ ድሪር /ግብጽ/ እና አምባሳደር አሊ አብዶ /ናይጀሪያ/ መንግስት የወቅቱን የሙስሊሙን ተቃውሞ አስመልክቶ የሚከተለው ስልት ትክክል እንዳልሆነ በግልጽ ማስቀመጣቸውንና መንግስት በአፋጣኝ አቋሙን እንዲያስተካክል ማሳሰባቸውን አመልክተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አምባሳደር አሊ አብዶ እና አምባሳደር ማህሙድ ድሪር ባለፈው ሳምንት ከክቡር ጠ/ሚንስትሩና ከአቶ ሽፈራው ጋር በስልክ መነጋገራቸውን አቶ ኃይለማርያም ገልጸዋል፡፡
- አዲስ አበባ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምበሲ የኢትዮጲያ ሙስሊሞች እያካሄዱት ባለው ተቃውሞ ዙሪያ ከውጭ ጉዳይ ጋር በቅርበት እየሰራ ካሉ የውጭ ድርጅቶች ዋናው መሆኑን፤ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሰፊ የምክርና የቴክኒክ ድጋፎች እየሰጠም እንደሚገኝ፤ ይሁን እንጂ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተቃውሞ ስፋትና ጥንካሬ እንዲሁም የሙስሊሙ ማህበረሰብ አንድነትና ቅንጅት ከፍተኛ ስጋት እንደፈጠረባቸው፤ ከኤምባሲው የምስራቅ አፍሪካ የደህንነት ጉዳዮች ኃላፊ ጋር ባለፉው አንድ ወር አቶ ኃይለማርያም በተደጋጋሚ በግል ተገናኝተው መወያየታቸውንና በመጨረሻ ባደረጉት አጠቃላይ ግምገማ ችግሩን በሰላማዊ መንግድ ለመፍታት የሙስሊሙ ተወካይ ከተባለው ኮሚቴ ጋር መነጋገር የተሻለ እንደሆነ መግባባት ላይ መደረሱን በመጨረሻም አሜሪካኖቹ በአፍሪካ ቀንድ ሌላ ተጨማሪ ቀውስ ማየት እንደማይፈልጉ በተደጋጋሚ እንደገለጹላቸው አቶ ኃይለማርያም በስፋት አብራርተዋል፡፡
- ተቃውሞው በተለይ ባለፈት ጥቂት ወራት የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ዋነኛ ስራ ሆኖ የቆየ መሆኑንና ሁሉም የውጭ የዲፕሎማቲክ ሚሽኖቻችን ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ በመስራት ላይ እንደሚገኙ፤ የተፈጠረው ችግር በተለይ በውጭ በሚኖረው የሙስሊሙን ህብረተሰብ ከፍተኛ ቁጣን እንዳስከተለና መንግስት ለችግሩ አፋጣኝ መፍትሄ እንዲሰጥ በመጠየቅ ላይ እንደሚገኙ፤
- አቶ ኃይለማርያም በመጨረሻም ከአንድ የሙስሊም ሀገር አምባሳደር ጋር በቅርቡ አዲስ አበባ ውስጥ በተካሄደው የኢኮኖሚ ፎረም ላይ ተገናኝተው የወቅቱን የኢትዮጲያ ሙስሊሞች እንቅስቃሴ አስመልክቶ መወያየታቸውንና ሰውየው በመጨረሻ "ጠቅላይ ሚንስትራችሁን ጨምሮ ሁላችሁም ወደ ቀድሞ አባቶቻችሁ አቋም እየተመለሳችሁ ይመስላል" ማለታቸውን አውስተው ብዙዎቹ የሙስሊምና የአረብ መንግስታት በችግሩ ላይ የመንግስትን አቋም በጥንቃቄ እየተከታተሉ እንደሚገኙ ያሚደርሷቸው መረጃዎች እንደሚያመለክቱ ገልጸዋል፡፡

**መከላከያ በጉዳዩ ላዩ የሰራቸው ስራዎች እንዲብራሩ ለቀረቡ ጥያቄዎች ለአቶ ሲራጅ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፡፡**

አቶ ሲራጅ በቅድሚያ ከቡር ጠ/ሚንስትሩ ይህንን አስቸኳይ የምክር ቤቱን ስብሰባ በመጥራታቸው ምስጋናቸውን ያቀረቡ ሲሆን ከአሁን በፊት በተካሄዱት የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ላይ በተለያዩ ምክንያቶች መገኘት አለመቻላቸውንና የእለቱ ስብሰባ በወቅታዊው የሙስሊሞች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ዙሪያ ሰፋ ያለ መረጃ ለማገኘት የረዳቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በሁሉም መስሪያ ቤቶች የቀረቡት ሪፖርቶች በችግሩ ዙሪያ እየተሰሩ ያሉትን ስራዎች ለማየት እንዳስቻላቸው፤ ሆኖም አንዳንድ የሰሟቸው ሪፖርቶች ያልጠበቋቸው መሆኑንና ጥያቄዎች እንዳስነሱባቸው አመልክተዋል፡፡ በተለይም አቶ ሽፈራው የኢትዮጲያ ሙስሊሞች የተፋጠነ እድገት የሀገሪቱን ብሎም በአፍሪካ ቀንድ ያለውን የኃይል ሚዛን ሊያዛባ እንደሚችልና በዚህም እድገቱ የተገደበ መሆን እንዳለበት ያነሱት ሀሳብ ግልጽ እንዳልሆነላቸውና እንዲህ አይነት ነገር ስለመኖሩም እንደማያውቁ ብሎም ይህ አይነቱ መግባባት መቼ፤ የት፤ ከማን ጋር፤ለምን፤ እንዳስፈለገ ጠ/ሚንስትሩ ተጨማሪ ማብራሪያ እንዲሰጡበት የጠየቁ ሲሆን በርግጥ የዚህ አይነት መግባባት ካለ አጠቃላይ የሙስሊሙን ማህበረሰብ እንቅስቃሴ በተመለከተ እንደ መንግስት አቋማችንን መለስ ብሎ መፈተሽ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡አቶ ሲራጅ ይህ የተጠቀሰው ስምምነት እጅግ አደገኛና ሀገሪቱ ለመገንባት ከምታስበው የዴሞክራሲ ስርአት ጋር አብሮ የማይሄድ፤ በህገ መንግስቱ የተረጋገጡ የሰብአዊ መብቶችና የሀይማኖት እኩልነትን የሚጻረር እንዲሁም ሀገራችንን በውጭ ሀይሎች ጉዳይ አስፈጻሚነት ሊያስፈርጃት የሚችል መሆኑን በስፋት ገልጸዋል፡፡

መከላከያ በችግሩ ዙሪያ በጣም ውስን የሎጂስቲክ ድጋፍ ለፖሊስ ከመስጠት ያለፈ ያከናወነው ምንም ስራ እንደሌለና በጉዳዩ ዙሪያ በተደረጉ ስብሰባዎች የሚንስትሩ ከፍተኛ አመራር ጉዳዩ ከመከላከያ ኃላፊነትና ማንዴት ውጭ መሆኑ ከስምምነት ላይ መደረሱን

አመልክተዋል፡፡ በመጨረሻም ጀነራል ሳሞራ የኑስን ጨምሮ ሌሎች አመራሮች በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በተለያዩ አጋጣሚዎች መግለጻቸውን አቶ ሲራጅ አመልክተዋል፡፡

በማስከተል አቶ ሙክታር በርካታ ሙስሊሞች መንግስተ ላለፉት ወራት ችግሩን ለመፍታት እየሄደበት ያለው አቅጣጫ ትክክለኛ የመንግስትን አቋም የማያንጸባርቅና በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያሉና የሙስሊሙን እድገት የማይሹ አንዳንድ ባለስልጣናትና ባለሙያዎች ለመንግስትና ህዝብ በሚሰጡት የተሳሳተ ምክርና መረጃ እንዲሁም በሚፈጥሯቸው መሰረተ ቢስ ስጋቶችና ማስፈራሪያዎች የመነጨ ነው የሚሉ ተደጋጋሚ ወቀሳዎች መስማታቸውንና አቶ ሽፈራውም ስራቸውን ነጻ በሆነ መንገድ እየሰሩ አይደሉም የሚሉ አቤቱታዎች ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመሩ መምጣታቸውን ገልጸው ይህም ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ውስጥ ስር እየሰደደ ከመጣው ሀይማኖታዊ ወገንተኝነት ጋር አብሮ ሊያዝ እንደሚችል አመልክተዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በፌዴራል ጉዳዮች የሚመራውና ይህንን ችግር በዋናነት የሚያስተባብረው ኮሚቴ ሀይማኖታዊ ስብጥር ምን እንደሚመስልና ከሀይማኖታዊ ወገንተኝነትስ ምን ያህል የጸዳ ነው ተብሎ እንደሚታመን ለቀረበው ጥያቄ ዶ/ር ሽፈራውን የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል፤

በቅድሚያ በእርሳቸውም ላይ ሆነ በሚኒስቴር መስሪያቤታቸው ላይ የሚወሩ እነዚህን የመሳሰሉ አሉባልታዎች የከፍተኛ አመራሩን ትኩረት አግኝተው በዚህ መድረክ ላይ መነሳታቸው እንዳሳዘናቸውና አቶ ሙክታር የጠቀሷቸውና ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች ተራ ውንጀላዎች በህዝቡና በመንግስት መካከል ልዩነት ለመፍጠር ብሎም በጉዳዩ ላይ በግምባር ቀደምትነት እየሰሩ ያሉ የመንግስት ባለስልጣናትን ተአማኒነት ለመናድ የሚደረጉ ሙከራዎች እንደሆኑ ጠቅሰው በርሳቸው በኩል ስራቸውን እየሰሩ ያሉት ከመስሪያ ቤታቸው ስልጣንና ሀኃፊነት አንጻር መሆኑን ተናግረዋል፡፡ሌሎቹም የሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው ኃላፊዎችና ሰራተኞች፣ እንዲሁም የተቋቋመው ጊዜአዊ ኮሚቴ ስራውን እየሰራ ያለው በተሰጠው ግልጽ የስራ ኃላፊነት መሰረት መሆኑንና የሃይማኖት ወገንተኝነት አለ ብለው እንደማያምኑ አመልክተዋል፡፡ የኮሚቴውን የሀይማኖት ስብጥር በተመለከተ ከሁሉም ሀይማኖቶች የተውጣጣ መሆኑንና በኮሚቴው ውስጥ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች እንዳሉ ሆኖም ኮሚቴው ሲዋቀር የስራ ብቃትና የድርጅት ታማኝነት እንጂ የሀይማኖት ስብጥር እንደመስፈርት እንዳልተወሰደ አመልክተዋል፡፡

**ችግሩ ምን ያህል የሀገር ውስጥና የውጭ ሚዲያዎችን ትኩረት ማግኘቱን በተመለከተ ለቀረበው ጥያቄ የሚከተለው መልስ ተሰጥቷል፡፡**
ችግሩ በተለይ ባለፉው አንድ ወር የበለጠ የሚድያ ሽፋን እያገኘ መምጣቱን፣ ከሀገር ውስጥ በዋናነት የኢትዮጲያ ቴሌቭዥንና ሬዲዮ ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው የፕሮፓጋንዳ ስራ እንዲሰሩ መመሪያ በተላለፉው መሰረት መጠነ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ስራ መስራቱ ተመልክቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የተለያዩ ሬድዮ ጣቢያዎች በተለይም ሬድዮ ፋና ለጉዳዩ ከፍተኛ ሽፋን በመስጠት የተለያዩ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀቱንና አብዛኛዎቹ ፕሮግራሞችም የመንግስትንና የመጅሊሱን አቋም የሚደግፉና የህዝብን ተቀባይነት ለማግኘት ታስበው የተዘጋጁ መሆኑ፣ ልዩ ልዩ የግል ጋዜጦች ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ጹሁፎችን መጻፋቸው፣ በግል ጋዜጦች ላይ የወጡት ጹሁፎች አንዳንዶች የመንግስትን አቋም የሚደግፉ ሲሆን ቀላል የማይባሉ ደግሞ የመንግስትን አቋም የሚጻረር መልእክት እንዳሳተላለፉ አቶ ሽፈራው የአንዳንዶቹን ጋዜጦች ስም በመጥቀስ አብራርተዋል፡፡

የውጭ ሀገር የሚድያ ሽፋንን በተመለከተ ተቃውሞው ቀላል የማይባል ሽፋን እንዳገኘ፣ ከቴሌቭዥን ጣቢያዎች አልጀዚራ የአረብኛና እንግልዝኛ ፕሮግራሞች፤ ቢቢሲ ቴሌቭዥን፣ ESAT የተፈጠረውን ችግር በቂ ሽፋን በመስጠት በተደጋጋሚ ዜናዎችና ፕሮግራሞች መስራታቸው እንዲሁም ከሬድዮ ጣቢያዎች ቪኦኤ፣ የጀርመን ድምጽ ራድዮ፣ ቢላልና ነጃሺ የተሰኙ የሙስሊም ሬድዮ ጣቢያዎች በችግሩ ዙሪያ ሰፊ ዘገባ ማቅረባቸው ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪ ልዩ ልዩ አለማቀፍ ጋዜጦች፣ መጽሄቶችና ጆርናሎች ከፍተኛ ሽፋን ሰጥተው ተቃውሞውን መዘገባቸው በተለያዩ የምክር ቤቱ አባላት ተገልጧል፡፡

ሌላው የሚዲያ አይነት ኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ሲሆን በዚህም የሙስሊሙ የወቅቱ ተቃውሞ ከፍተኛ ሽፋን አንዳገኘና የተለያዩ ዌብ ሳይቶች እንዲሁም ፌስቡክ እና ፓልቶክ በመሳሰሉ የማህበራዊ ሚዲያዎች ጉዳዩ በከፍተኛ ሁኔታ የመነጋገሪያ አጀንዳ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ አቶ ጌታቸው ከሚዲያ ጋር በተያያዘ በሰጡት ተጨማሪ መግለጫ የሙስሊሙ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ከተጀመረ በኋላ የሀገራችን የፌስቡክ፣ የፓልቶክ እንዲሁም የሌሎች ሚዲያ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች በብዙ እጥፍና በሚያስደንግጥ መጠን ማደጉን ገልጸዋል ቴክኖሎጂው በሀገር ደህንነት ላይ ሊፈጥር የሚችለውን አሉታዊ ተጽኖ ለመቀነስ መስሪያ ቤታቸው ከየኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ /ኢንሳ/ ጋር በመተባበር አንዳንድ ስራዎችን በመስራ ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር ተቃውሞው በዋናነት እየተመራ ያለው በፌስቡክ ላይ በሚሰጡ መልእክቶች መሆኑና በተለይም ድምጻችን ይሰማ የተሰኘው ገጽ ተቃውሞውን በዋናነት እየመራ እንደሚገኝ ብሎም ይህንኑ ገጽ ለመዘጋት የተደረጉ ሙከራዎች እንዳልተሳኩ አመልክተዋል፡፡

**ማጠቃለያ**
ከላይ በቅደም ተከተል በቀረበው መሰረት የኢትዮጲያ ሙስሊሞች ከ2004 መባቻ ጀምሮ ያነሷቸውን ጥያቄዎች አስመልክቶ የብሄራዊው ደህንነት ምክር ቤት አባላት በስፋትና በጥልቀት ከተወያዩ በኃላ ሂደቱ ጠቅለል ብሎ ሲታይ መንግስት ችግሩን ለመረዳት የሄደባቸው ስልቶችና የተጠቀመባቸው የመረጃ ምንጮች የተዛቡ መሆናቸውና የመንግስት አካላት ችግሩን ለመፍታት ሲከተሏቸው

የነበሩት አቅጣጫዎችና የወሰዷቸው እርምጃዎች በትክክለኛ መረጃ ላይ ያልተመሰረቱና ባብዛኛው የተሳሳቱ እንደነበሩ በምክር ቤቱ አባላት መካከል መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ የተነሱት አንኳር ነጥቦች እንደሚከተለው ተጠቃለዋል፡፡

1) ሙስሊሞች ያነሱዋቸውን ጥያቄዎች በትክክልና በቅንነት ለመረዳት የተደረገ በቂ ሙከራ አለመኖሩ፤ በዚህም ምክንያት የችግሩን እውነተኛ ይዘት ለመረዳትና ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት አለመቻሉ፤
2) መንግስት ለተፈጠረው ተቃውሞ እና ባጠቃላይ ለህዝበ ሙስሊሙ የሰጠው ግምት የተሳሳተ እና እጅግ ዝቅተኛ መሆኑ፤
3) ችግሩ ከግዜ ወደ ግዜ እየሰፋ መምጣቱ፤ አፋጣኝና ትክክለኛ መፍትሄ ካልተሰጠውም ይበልጥ እየተወሳሰበ እንደሚሄድና አሁን ያለው ፍጹም ሀይማኖታዊ ጥያቄ መልኩን ቀይሮ ፖለቲካዊ ወይም ሌላ ሊሆን እንደሚችል፤
4) ከተቃውሞው ጋር በተያያዘ በመንግስት በኩል የተፈጠረው ስጋት መሰረት እንዳልነበረውና መንግስት የወሰዳቸውም አብዛኞቹ እርምጃዎች ባልተረጋገጡ ስጋቶች ላይ የተመሰረቱ እንደነበሩ፤
5) ሙስሊሞች ያነሷቸውን ጥያቄዎች ለመመነስ በተለይ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትርና መጅሊሱ የተጠቀሙባቸው ስልቶች ሙስሊሙን ማህበረሰብ ይበልጥ እንዳስቆጡና ተቃውሞውንም እንዲባባስ ማድረጋቸው፤
6) በስራ ላይ ያሉት የኢትዮጲያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት አመራር አባላት የመጅሊሱን ህግና ደንብ በሚጻረር መልኩ ያለምርጫ ወደ ስልጣን የመጡና በስልጣን ላይ መቆየት ከሚገባቸው የጊዜ ገደብ በላይ መቆየታቸው አግባብ አለመሆኑና በአፋጣኝ ምርጫ እንዲካሄድ የተነሳው የህዝብ ጥያቄ ተገቢ መሆኑ፤
7) ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር በተፈጠረው አለመግባባት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ የነበረውን ተቀባይነትና ታማኝነት ሙሉ ለሙሉ እንዳሳጣው፤
8) የተነሳው ተቃውሞ ህጋዊና አላማውም ሀይማኖታዊ ብቻ መሆኑ፤ የውጭ እጅም ሆነ ድብቅ የፖለቲካ አላማ እንደሌለውና ከማናቸውም አይነት ጸረ-ሰላም እንቅስቃሴዎች ጋር ግንኙነት እንደሌለው፤
9) ህዝበ ሙስሊሙ ተቃውሞውን እየገለጸበት ያለው መንገድ እጅግ ሰላማዊና በሰለጠነ ሁኔታ በመካሄድ ላይ መሆኑ፤
10) በተለይ ግንቦት ስስት በዋለው የእርብ የጸሎት ስነ-ስርአት አከባበር፤ በእለቱ አዲስ አበባ ውስጥ ይካሄድ የነበረውን አለማቀፍ የኢኮኖሚ ፎረም ከግምት ውስጥ በማስገባት ህዝበ ሙስሊሙ ተቃውሞውን በዝምታ እንዲያሰማ የተወሰነው ውሳኔና አፈጻጸሙ ፍጹም ኃላፊነት የተሞላበትና ሊመሰገብ የሚገባው ሁኔታ መሆኑ ተጠቅሷል፡፡

**የውይይቱ ማጠቃለያ ሀሳቦች ከቀረቡ በኃላ ማጠቃለያ ሀሳቦቹን መሰረት በማድረግ የመፍትሄ ሀሳቦች እንዲቀርቡ ክቡር ጠቅላይ ሚንስት ጠይቀዋል፡፡ ሆኖም ግን የመፍቴ ሀሳብ ከመስጠቱ በፊት ዶ/ር ሽፈራው የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡**

ዶ/ር ሽፈራው ቀደም ብለው በተቀመጡ የማጠቃለያ ሀሳቦች በመሰረተ ሀሳብ ደረጃ ሊስማሙ እንደሚችሉና በሁሉም የመንግስት አካላት አንዳንድ የግንዛቤ ችግሮች እንደነበሩ ብሎም አንዳንድ የአፈጻጸም ግድፈቶችም ሊኖሩ እንደሚችሉ መቀበል ተገቢ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ይሁን እንጂ መንግስት እስካሁን የሄደበት አቅጣጫና የወሰናቸው ውሳኔዎች ምንም አይነት የመርህና የስትራቴጂ ችግር እንደሌለባቸው በግላቸው እንደሚያምኑና የተፈጠረው ችግር ከአጠቃላይ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር የተፈጠረ ችግር ተደርጎ ድምዳሜ ላይ እንዳይደረስ አሳስበዋል፡፡ ዶ/ር ሽፈራው አሁንም ቢሆን ችግሩ ጥቂት አክራሪዎች በሰፊው ሙስሊም ህዝብ ስም እየፈጠሩት ያለ ችግር እንደሆንና የዚህ አይነቱ የአክራሪነት አደጋ ሀገሪቱን ወዴት ሊወስድ እንደሚችል ጎረቤት ሶማሊያን ማየት በቂ እንደሆን አሳስበዋል፡፡ በዚህም የተሰጡት ማጠቃለያዎች እንዳሉ የሚወሰዱ ከሆን የፌዴራል ጉዳዮች ሚንስቴርም ሆነ ሌሎች የመንግስት አካላት እስካሁን ሲሄዱበት ከነበረው አቅጣጫ ሙቶ ሰማንያ ዲግሪ ሊያዞራቸው እንደሚችልና በዚህ ፍጥነትና መጠን የአቅጣጫ ለውጥ ማድረግ የመንግስትን የውሳኔ አሰጣጥ ስርአት ጥያቄ ውስጥ ከማስገባቱም ባሻገር ለውጡ በመንግስትም ሆነ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አሉታዊ ጎን ቆም ብሎ ማሰብ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

በመቀጠል ክቡር ጠ/ሚንስትሩ ዶ/ር ሽፈራው ያነሷቸውን ሀሳቦች በተወሰነ ደረጃ የሚጋሯቸው ቢሆንም ችግሩን ለመፍታት ከዚህ ሌላ የተሻለ አማራጭ መንግስት ሊኖረው እንደማይችል አመልክተዋል፡፡ ክቡር ጠ/ሚንስትሩ መንግስት ከአሁኑ ስህተቱን ተቀብሎ ማስተካከል ካልቻለ ጉዳዩ ወዴት ሊሄድ እንደሚችል መገመት እንዳማያዳግትና ችግሩን ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. መርሆዎችና ታሪክ አንጻርም ማየት እንደሚያስፈልግ የገለጹ ሲሆን ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ዋናዋና ባህሪያት ውስጥ ስህተትን አምኖ መቀበል ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን፤ ከዚህ አንጻር ቀውሱ ወደባሰ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ስህተትን መቀበልና ማረም ብሎም ከህዝበ ሙስሊሙ ጋር የመንግስትንና የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ.ን ግንኙነት ማደስ ተገቢ መሆኑን በማስረዳት የመፍትሄ ሀሳቦች እንዲሰጡ አባላቱን ጠይቀዋል፡፡

**የውሳኔ ሀሳቦች**

ከላይ የተጠቀሱትን ውይይቶችና የማጠቃለያ ነጥቦች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የውሳኔ ሀሳቦች ተወስደዋል፡፡

1. የአህባሽ አስተምሮትና ስልጠናዎች በአፋጣኝ እንዲቆሙ፣
2. የአወሊያ ትምህርት ቤት አደረጃጀትና የባለቤትነት ጥያቄ ህዝቡ በሚፈልገው መልኩ እንዲፈጸም፣
3. የመጅሊስ አመራር አባላት ምርጫ ግልጽና ህዝበ ሙስሊሙ በሚፈልገው መልኩ በአፋጣኝ እንዲፈጸም፣
4. ችግሩን ያባብሳሉ ተብለው የሚገመቱ ተዛማጅ ጉዳዮች በአፋጣኝ እንዲታዩና አስፈላጊ የማስተካከያ ስራ እንዲሰራ፣
5. የዘምዘም ባንክ ቀደም ሲል በተሰጠው ፍቃድ መሰረት የምስረታ ሂደቱ ተጠናቆ በአፋጣኝ ስራ ይጀምር ዘንድ የብሄራዊ ባንክ አስፈላጊውን እንዲያደርግ፣
6. በመንግስት ሚዲያዎች ችግሩን አስመልክቶ የሚዘጋጁ ፕሮግራሞች ይዘት አፋጣኝ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው፣ በተለይም የኮሚቴውን አባላት በተመለከተ የሚተላለፉ መልእክቶች እንዲታረሙ፣

7. ህዝብ ከመረጣቸው የኮሚቴ አባላት ጋር ቀደም ሲል የተጀመረው ውይይት እንዲቀጥልና ችግሩ በአጭር ግዜ ውስጥ እንዲቋጭ አስፈላጊው እንዲደረግ፣
8. ችግሩ በውጭ ግንኙነት ላይ የፈጠረውን አላስፈላጊ ብዥታ ለማስተካከል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የራሱን እቅድ ነድፎ እንዲንቀሳቀስ፣
9. በችግሩ ጋር በተያያዘ የታሰሩ ካሉ በአፋጥኝ እንዲለቀቁ፣
10. በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባላት መካከል የተከሰተውን ተቃውሞ ለማስተካከል በየደረጃው ስራዎች እንዲሰሩ ለዚህም የሚረዱ ሰነዶች እንዲዘጋጁ፣
11. ሌሎች ዝርዝር የማስተካከያ ስራዎችን በፌደራል ጉዳዮች ሚ/ር አስተባባሪነት እንዲሰሩና እንዲፈጸሙ ተወስኗል፡፡

በመጨረሻም ጠቅላይ ሚንስትሩ ለአስቸኳይ ህክምና ወደ ውጭ ሀገር እንደሚሄዱና ህክምናቸውን ጨርሰው እንደተመለሱ የውሳኔዎቹን አተገባበር እንደሚገመግሙ በመግለጽ ስብሰባው ከሌሊቱ ሰባት ሰአት ተኩል ተጠናቋል፡፡